# በሀገሩ የሚቀልደው ተቃዋሚና የግሉ ጋዜጠኛ

ዋለልኝ ድንቁ

07/04/14

የተቃዋሚው የፖለቲካ እይታው አድማስ ከዓመት ዓመት ማደግና መሻሻልን ሳይሆን እየወረደም እየዘቀጠም ነው፡፡ የዓለም ጂኦ ፖለቲካዊ ለውጥና የፖለቲካ ሂደት ፍፁም ወደማይመለስበት ከዚህ በፊትም ታይቶ ወደማይታወቅ አዲስ አቅጣጫ እየነጎደ ይገኛል፡፡

ለወትሮው የምዕራቡና የምሥራቁ ዓለም ይባል ከነበረው የፖለቲካ ኢኮኖሚ አስተሳሰብ የወጣ አዲስ ክስተት በቀዳሚ የፖለቲካ መድረኩን ተቆጣጥሮታል፡፡ ይህም የዓለም አቀፍ አክራሪ እስላማዊ ኃይሎች (ጅሀዲስት ኃይሎች) ከዚህም ጋር ተያይዞ በዓይነቱ የተለየ አሸባሪነት በፍጥነት እየተዛመተ በመምጣቱ ነው፡፡

ይኸው እንደ ሰደድ እየተቀጣጠለ የሚስፋፋው እስላማዊ አክራሪና አሸባሪ ኃይል ምዕራቡን፣ ምሥራቁን ቀሪውንም ሰሜንና የደቡቡን ዓለም በእጅጉ እየናጠው እያሳሰበውም ይገኛል፡፡ የፖለቲካና የኢኮኖሚ መርሆዎች ልዩነት ቢኖራቸውም ጅሀዲስትና አሸባሪዎችን በተመለከተ ምዕራቡም ምሥራቁም ዓለም የግዴታ የሚተባበሩት ሁኔታ ተፈጥሯል፡፡

የእኛ ተቃዋሚዎች ደግሞ ገና እያሾፉ፣ እየቀለዱና እየተሳፈጡ ናቸው፡፡ መንግሥት በኢትዮጵያ እስላማዊ አክራሪነትና ኃይማኖታዊ ፖለቲካ ግባቸውን አስመልክቶ እጅግ አረመኔና ኢሰብዓዊ የሆነ የጥፋት ኃይል እንቅስቃሴ መኖርን በተጨባጭ ማስረጃ ሲናገር በዚህም ለሕዝቡ ሲያሳውቅ (ዶክመንተሪ) ፊልም ሲያቀርብ የእኛ ተቃዋሚዎች ያጣጥሉታል፣ ያንቋሽሹታል፡፡

መንግሥት በኃይማኖት ጉዳይ ገለልተኛ እንደሆነ ሕገ መንግሥቱ ቢደነግግም ጣልቃ ገብቷል፣ የሙስሊሙን መፍትሄ አፈላላጊዎች አስሯል ከማለትም አልፈው የአክራሪውን እስላማዊ ኃይል ደጋፊዎች ወደተቃዋሚው ደጋፊነትና ተባባሪነት ለማሰለፍ ጥረት አድርገዋል፤ እያደረጉም ይገኛሉ፡፡

የሰማያዊ ፓርቲ የተቃውሞ ሰልፍ ዋነኛው አጋር ኃይል የፅንፈኛው አክራሪ ቡድን ደጋፊዎችና አቀንቃኞች ነበሩ፤ ናቸውም፡፡ የሀገር ውስጡና ጽንፈኛው ተቃዋሚ ጉዳዩን በጥልቀት ሳይመረምር ከአክራሪው ጐን መሰለፍና መቆምን መርጧል፡፡

በእድሜ አዛውንት የ80 ዓመት ሽማግሌ የእርቅና ሠላም አስተማሪ የነበሩት የደሴው ሼህ ቤታቸው በራፍ በአክራሪዎች ጥይት ተደብደበው ሲሞቱ የሀገር ውስጡም ሆነ በውጭ ያለው ፅንፈኛው ተቃዋሚ ለምን እንዲህ ዓይነት ይደረጋል፤ አሸባሪነት ነው ብሎ ተቃውሞውን አላሰማም፡፡

ካዋራጃ የተባለው እስላማዊ አክራሪ ኃይል ወታደራዊ ክንፍ አደራጅቶ መሣሪያ ታጥቆ እስላም ክርስቲያን ሳይል ዜጐችን ሲገድል፤ መስጊድና ቤተክርስቲያን ሲያቃጥል ይኼ ጉዳይና አዝማሚያው ለሀገርና ለሕዝብ ሠላምና ደህንነት ለአብሮነት የሚበጅ አይደለም፤ የአሸባሪነት መገለጫ ነው ብሎ አልተቃወምም፡፡

አልሸባብ በምሥራቅ አፍሪካ ሀገሮች አካባቢ የአልቃይዳ ቅርንጫፍ ሆኖ በኬንያ ተደጋጋሚ አደጋ እያደረሰ፤ በኢትዮጵያ ላይም ተደጋጋሚ ጅሀድ ማወጁን እየገለፀ ባለበት በአሁኑ ወቅት የሀገር ውስጡና በውጪ የሚገኘውም ፅንፈኛ ተቃዋሚ አልሻባብን በአሸባሪነት በፅንፈኛ እስላማዊ አክራሪነት አልፈረጁትም ወይንም ይህ በሀገርና በሕዝብ ላይ የተቃጣ አደጋ ነው ብለው ተቀውሟቸውን አላሰሙም፡፡ እነዚህ ሰዎች ሌላ ሀገር አላቸው ማለት ነው ያሰኛል፡፡

የአፍሪከ ሕብረት፤ የአውሮፓ ህብረት፤ የምዕራቡም የምሥራቁም ዓለም የአልሸባብን የአልቃይዳ ክንፍ መሆንና ዓለም አቀፍ አሸባሪነቱን በማስረጃ አረጋግጠው እየተዋጉ ባሉበት፤ የኢትዮጵያ ሠራዊትም የአፍሪካ ሠላም አስከባሪ ኃይል አካል በመሆን አልሸባብን እያሳደደ መስዋዕትነት እየከፈለ በመምታት ላይ በሚገኝበት በዚህ ወቅት ጭርሱንም የኢትዮጵያ ተቃዋሚ ኃይሎች የኢትዮጵያ ሠራዊት ለምን በሶማሊያ ገብቶ ይዋጋል በሚል ጠንካራ ተቃውሞ ያሰሙበት ጊዜም ነበር፡፡

ይህን የእስላማዊ አክራሪነት አደጋ አንድም ቀን በአንድም አጋጣሚ የሀገር ውስጡም የዲያስፖራውም ፅንፈኛ የተቃወሙበት ጊዜ የለም፡፡

ይህ ብቻ አይደለም፡፡ እንዲያውም መንግሥት አሸባሪነትንና እስላማዊ አክራሪነትን በመጠቀም የፖለቲካ ተቀናቃኞቹን ያስራል የሚል ጩኸት ያሰማሉ፡፡ አሸባሪነትና አክራሪነት (የኃይማኖት) በሁሉም ዓይነት ኃይማኖቶች ውስጥ ያለና የሚከሰት ነው፡ አስከፊ የሚያደረገው ወደ ተግባራዊ ጥፋት ሲሰማሩ፤ ሕዝብን በጅምላ ሲገድሉና ሲፈጁ፤ መሠረታዊ ልማቶችን ሲያውድሙ፤ የሀገርን ሠላምና ፀጥታ ሲያናጉ ነው፡፡

አሸባሪነትና አክራሪነት ሥርዓተ አልበኝነትና አለመረጋጋት እንዲሰፍን በማድረግ የዓለምን ሕዝብ ህይወት ባልተጠበቀ ፈጣን አደጋ ውስጥ ከቶታል፡፡ ሶማሊያ፣ ኬንያ፣ ናይጄሪያ፣ ሶሪያ፣ ሊቢያ፣ ግብፅ፣ አፍጋኒስታን፣ ፓኪስታን አሁን ደግሞ በአዲስ መልኩ በሺያዎችና በሰለፊዎች (አይሲስ) ፅንፈኛ አክሪሪዎች በደም እየታጠበች ያለችውን ኢራቅ መመልከት ይቻላል፡፡

በእነዚህ ሀገራትና በሌሎችም እስላማዊ አክራሪነትና አሸባሪነት አሜሪካና እንግሊዝን ምዕራቡን ዓለም በሙሉ ባስደነገጠና ከቁጥጥራቸው ውጪ በወጣ ሁኔታ ለመስፋፋትና የዓለም አስጊ ኃይል ለመሆን የበቃው በአብዛኛው የቀለም አብዮት ተብለው በምዕራባውያን የኒዮ ሊበራል ኃይሎች በሚሊዮኖችና ቢሊዮኖች በዓለም ዙሪያ በፈሰሰው ገንዘብ  ነው፡፡

በየሀገሩ ያለውን ተቃዋሚ በመርዳት ጠንካራ መንግሥታት እንዲፈርሱና እንዲበተኑ በማድረጋቸው ይህን ተከትሎም የመንግሥታዊና የደህንነት መዋቅሮች መፈራረስና የተረጋጋ መንግሥት መፈጠር አለመቻሉ፤ በተፈጠረውም ሥርዓተ አልበኝነት እጅግ ዘመናዊ የሆኑ ቀላልና ከባድ መሣሪያዎች በተለያዩ አሸባሪ የጅሀድ ኃይሎች በአልቃይዳና በሌሎችም እጅ እንደልብ ሊገባ በመቻሉ ነው፡፡

ምዕራባውያኑ የለኮሱት የሰደድ እሣት ባሰቡትና ባቀዱት የሂሳብ ቀመር ሳይሆን ውጤቱ ያልታሰበውን አደጋ በእነሱው ላይ ይዞ ከተፍ አለ፡፡ አሁን በአጠቃላይ ማጣፊያው እስኪያጥራቸው ድረስ የእነሱን ጭንቀት አበርትቶታል፡፡

በአፍጋኒስታን በሶሪያ በተለይም አሁን በኢራቅ ከሱኒው የኢይሲሲ አክራሪ የጅሀድ ኃይል ጋር አብረው የተሰለፉ ወደ ሁለት ሺህ የሚጠጉ የአውሮፓ ዜጐች እንዳሉ የመረጃ ምንጮች ይጠቁማሉ፡፡ እንግሊዛዊ ዜግነት ያላቸው መኖራቸውም ታውቋል፡፡

መሐንዲሶች፣ ሣይንቲስቶች የተለያየ ሙያ ያላቸው ምሁራን እንዳሉ ዓለም አቀፍ የመረጃ ተቋማት ይመሰክራሉ፡፡ የናይጄሪያው ቦኮ ሀራም አባላት አብዛኛዎቹ ባለዲግሪዎች እንደሆኑ ቢቢሲ በዘገባው ገልጿል፡፡

አሸባሪነትና እስላማዊ አክራሪነት ዘር፣ ጐሣ፣ ፆታ፣ ቀለም፣ ሙያ አይለይም፡፡ ምንጩ የከፋ ጥላቻ ነው፡፡ አሸባሪነትና እስላማዊ አክራሪነት ፀረ ዴሞክራሲ፣ ፀረ ልማት፣ ፀረ ሠላም፣ ፀረ ሥልጣኔ፣ በእልቂትና በከፋ የደም መፋሰስ የሚያምን የሀገርም የሕዝብም እጅግ የከፋው አቻ የማይገኝለት ጠላት ነው፡፡ ከእነሱ አስተሳሰብ ውጪ ያለ ማንኛውም ሰው፤ ወጣት፣ አሮጊት፣ ሽማግሌ ሆነ ሕፃናት ሳይሉ በፍፁም አረመኔነት የሚገሉ የሚጨፈጭፉ ናቸው፡፡

በዘረኝነትም ሆነ በኃይማኖታዊ አክራሪነት የሚነሱ ኃይሎች የመጨረሻ ግብ እልቂትና ደም መፋሰስን እውን ማድረግ በመሆኑ አሸባሪዎች ናቸው፡፡ ፅንፈኛ የፖለቲካ አክራሪዎችም ቀጣዩ ግባቸው ከእነሱ በእምነትና በአስተሳሰብ የተለየውን ሁሉ ማጥፋትና በጠመንጃም ሆነ በማንኛውም ኃይል ማስወገድ ስለሆነ እነዚህም በአሸባሪነትና በፍፁም ፋሽስታዊ አቋም ውስጥ የሚመደቡ ናቸው፡፡

እንደ ሌሎች የሙያ መስኮች ሁሉ የሕግ ሰዎች፣ ኢንጂነሮች፣ ሣይንቲስቶች ሌሎችም በአሸባሪነት ውስጥ ተዘፍቀው የመገኘታቸውን ያህል በጋዜጠኝነትም ሙያ ውስጥ የነበሩም ያሉም አሸባሪ ሆነው የተገኙበት የሚገኙበትም አጋጣሚ አለ፡፡

በቅርቡ የግብፅ ፍርድ ቤት አሸባሪነትና አክራሪነትን በማራመድ ለብዙ ሕዝብ እልቂትና ለሀገር ውድመት ምክንያት ለሆነው የግብፁ ሙስሊም ብራዘር ሁድ ዓላማ መሳካት በተግባር ደግፈዋል፤ በሂደቱም ተሳትፈዋል ባላቸው የአልጀዚራ (የእንግሊዝና የሌላም ሀገር ዜግነት ያላቸው) ጋዜጠኞች ላይ የዓመታት የእሥር ፍርድ ሰጥቷል፡፡

ይሁንና ቅጣቱ ዓለም አቀፍ ተቃውሞ ቢያስነሳም ከሀገሬ ሠላምና ደህንነት በላይ ምንም የለም የሚለው የግብፅ መንግሥት በፍርድ ቤቶች ውሣኔ ጣልቃ አልገባም ብሏል፡፡

የአሸባሪና የአክራሪዎችን ዓላማ በሕዝብ ዘንድ በማሰራጨትና በማድረስ የበለጠ እልቂትና ጥፋት እንዲደርስ በማድረግ ረገድ ዋነኛውን ሚና የሚጫወቱት ሚዲያዎችና ጋዜጠኞች መሆናቸው በተደጋጋሚ ተረጋግጧል ብሏል፡፡

የእኛን ሀገር የመሰለው በአብዛኛው ደረጃው የወረደ፤ በምክንያታዊነትና በጭብጥ በማስረጃ የማያምን፤ በጥላቻን አሉባልታ የተሞላ፤ በገንዘብ እየተገዛ ሀገርና ሕዝብን ለማተራመስ ለሚተጉ ኃይሎች በፍፁም መሣሪያነት የቆመ የግል ፕሬስ የአሸባሪነትን ዓላማ በሥውር ከሚያራምዱ ኃይሎች ጋር ተሰልፎ ልሣናቸው ሆኖ ከበሮ እየደለቀ ይገኛል፡፡

ኢሕአዴግን የሚቃወሙ የፖለቲካ ቡድኖች በተለይ ከፅንፈኛውም ሆነ ከየትኛውም ኃይል ጎን ተሰልፈው ከሥልጣን እናወርደዋለን ሲሉ የሚደሰኩሩት፤ ከአልሸባብና ከአልቃይዳም ጋር ሆኖ ኢትዮጵያ ውስጥ ትጥቅ ትግል ለማካሄድ ሲል ከተመታው አክራሪ እስላማዊ ቡድንና ከሻዕቢያም ጋር እንደሚሰለፍ በዘወርዋራም መግለጹ ነው፡፡ ይህም በሥራ ላይ ካሉት ጥቂት ኃላፊነት ከሚሰማቸው የግሉ ጋዜጦች በስተቀር አብዛኛው የግሉ ፕሬስ መጽሄትና ጋዜጣ ካለበት ከፍተኛ የገንዘብ ችግር አንፃር የአሸባሪዎች መሣሪያ አይሆኑም፤ ዓላማቸውን በማሰራጨትና በማዛመት አይሰሩም ለማለትም አይቻልም፡፡

በዚህ መልኩ ዛሬ በሌላው ዓለም በተጨባጭ እየታየ እንዳለው ጋዜጠኞች የአሸባሪዎችን እምነት፤ አስተሳሰብና የፖለቲካ ዓላማ እስካሰራጩና እስካራመዱ ድረስ በአሻባሪነት ተፈርጅው ፍርድ ቤት ቀርበው መቀጣታቸው ግድና አይቀሬ መሆኑን የግብፅ ችሎት በቅርቡ ለዓለም አሳይቷል፡፡

ተቃውሞው ቢበረታም የግብፅ መንግሥት ከሀገሬ ሠላምና ደህንነት በላይ አጀንዳ የለኝም፤ ለደረሰው ጥፋት ጋዜጠኞቹ የሚገባቸውን ፍርድ አግኝተዋል ብሏል፡፡ የእኛዎቹ የግሉ ፕሬስና ተቃዋሚው ቡድን የእስላማዊ አክራሪዎችን አጀንዳ ሕጋዊና ሠላማዊ አድርጎ እያራገበው ይገኛል፡፡ እናም በሀገር ፀጥታና በሕዝብ ደህንነት ላይ ለሚደርሰው ጥፋት ኃላፊነቱን ሊሸከም ግድ ይሆናል፡፡